

# ፍርድ እንደ ፈራጁ

**ለአፄ ቴዎድሮስ፦**

ፍየሏን ያየው ሕዝብ ተሻግራ ስትሄድ፣
ለማመልከት ብሎ በመሄድ መሪው ዘንድ፣
“ባሕር አቋረጠች ተሻግራ በረረች፣
ኧረ ምን ተሻለ ፍየሏ’ኮ ሄደች ?”
ብሎ ቢነግራቸው ለመይሳው ካሣ፣
ቱግ አለ ደማቸው ቁጣቸው ተነሳ፦
“ለመሄድ ለመሄድ ኧረ ትሂድ የትም፣
አገሩ የኛው ነው እስከ እረሩሳሌም፣
ግን እጅ ሳትነሳኝ ባሕር መሻገሯ፣
በዚያ ላይ አፈሬን ተሸክማ በእግሯ፣
እንዴት ብትደፍረኝ ነው ጥላኝ መኮብለሏ!
ቶሎ ትያዝና ቤት ተዘግቶባት፣
ሁለት የፊት እግሯ ይቆረጥባት።
ምላሷም ከበዛ በዚችም ቅጣት፣
ቤቱ እንደተዘጋ ትቃጠል በእሳት።”
ብለው በመደምደም ፍርዳቸውን ሰጡ፣
እንደ ፈራጁ እንጂ መች እንዳመጣጡ።



**ለአፄ ዮሐንስ፦**

“ባሕር አቋረጠች ተሻግራ በረረች፣
ኧረ ምን ተሻለ ፍየሏ’ኮ ሄደች ?”
ብሎ ቢነግራቸው ለአፄ ዮሐንስ፣
ነገሩን አጢነው በማለሳለስ፦
“ግብር እስከገበረች ለእኔው እስካደረች፣
ተዋት ነፃ ትሁን ግዛት ታሰፋለች።
እንዴውም ስላሰብኩ ልሾማት ንግሥና፣
አንዲት ነገር ብቻ ኑልኝ አጣሩና፣
ይህች ፍየል ስትሄድ ከሃገር እርቃ፣
ማተብ አርጋለች ወይ ሐይማኖቷን አውቃ?
ይህን ካላረገች አንገቷን ቅሉልኝ፣
በአንካሴ ውጉና እራሷን አምጡልኝ።”
ብለው በመደምደም ፍርዳቸውን ሰጡ፣
እንደ ፈራጁ እንጂ መች እንዳመጣጡ።



# ፍርድ እንደ ፈራጁ

ለአፄ ምኒሊክ፡-

“ባሕር አቋረጠች ተሻግራ በረረች፣

ኧረ ምን ተሻለ ፍየሏ'ኮ ሄደች ?”

ብሎ ቢነግራቸው ለአፄ ምኒሊክ፣

ወዲያው አዋጅ ሰርተው ለሕዝቡ በመላክ፡-

“ፍየሏ እንደፍልፈል ፈልፍላ ፈልፍላ፣

ባዕድ መሆኗ ነው አልፈልግም ብላ፣

ክተት ዝመት ሕዝቤ እኔ የምወድህ፣

ይህን ጉድ በቶሎ መመለስ አለብህ፣

ወስልተህ ብትቀር ግን ላልምርህ ማሪያምን፣

መነኮሳቶቼም በፀሎት አትርሱን፣

ፍየሏ ሰልጥና ብትተኩስብህ፣

በቅዝምዝም ጣላት በጦር በጎራዴህ።”

ብለው በመደምደም ፍርዳቸውን ሰጡ፣

እንደ ፈራጁ እንጂ መች እንዳመጣጡ።



ለአቤቶ እያሱ፡-

“ባሕር አቋረጠች ተሻግራ በረረች፣

ኧረ ምን ተሻለ ፍየሏ'ኮ ሄደች ?”

ብሎ ቢነግራቸው ለአቤቶ እያሱ፣

የፌዝ ሳቅ በመሳቅ በንቀት መለሱ፡-

“አይ ሸዌ ሸውሻዌ ወሬ ስትዶልቺ፣

በፍየል አሳበሽ ሤራሽን ልትመቺ፣

ምኒስትር ተብዬ የአያቴ አሽከር ሁላ፣

ብትንትን አድርጌሽ ባልተካሽ በሌላ!

ሆዳችሁ አባጣ ቂጣችሁ ዘርባጣ፣

ምን ትሰሩ ነበር ፍየሏ እስክትወጣ?

በጥጋብ ዘመኔ በተትረፈረፈው፣

የፍየል መኮብለል ትርፉ ለመራብ ነው፣

ቲኒሽ ችግር ስትቀምስ ትመለሳታለች፣

አገር አታገኝም የኛን የመሰለች።”

ብለው በመደምደም ፍርዳቸውን ሰጡ፣

እንደ ፈራጁ እንጂ መች እንዳመጣጡ።



# ፍርድ እንደ ፈራጁ

ለአፄ ኃይለ ሥላሴ፡-

“ባሕር አቋረጠች ተሻግራ በረረች፣
ኧረ ምን ተሻለ ፍየሏ'ኮ ሄደች ?”
ብሎ ቢነግራቸው ለኃይለ ሥላሴ፣
አሰብ አረጉና ቲኒሽ በትካዜ፡-
“የዓለም ህዝብ ይወቀው ይህን ዕኩይ ሥራ፣
እዚያብሔር ይፈርዳል ሰው እንኳን ቢፈራ፣
በጠራራ ፀሐይ ሕግ በማይፈቅደው፣
ፍየሏ ሄዳ አትቀር ድሉ ጊዜያዊ ነው፣
እኛ የምንወድህ ጀግናውም ሕዝባችን፣
ተግተህ ታገልና ትምጣ ፍየላችን፣
ፍየሏ ስትመጣም በጥሩ እንድትለምድ፣
ተመቻችት እንጂ አትያዛት በግድ።”
ብለው በመደምደም ፍርዳቸውን ሰጡ፣
እንደ ፈራጁ እንጂ መች እንዳመጣጡ።



ለጓድ መንግሥቱ፡-

“ባሕር አቋረጠች ተሻግራ በረረች፣
ኧረ ምን ተሻለ ፍየሏ'ኮ ሄደች ?”
ብሎ ቢነግራቸው ለጓድ መንግሥቱ፣
ከቁጣቸው ብዛት ጠበበ መሬቱ፡-
በአድሀሪ ኮብላይ የፍየል ወጠጤ፣
እርምጃ ይወሰድ ይቺ አፈ ቀላጤ፣
እኛ ካለ ፍየል ለመኖር አንችልም፣
የእናት ሀገራችን ህልውና አይኖርም፣
አንድ ጥይት እና አንድ ሰው እስኪቀር፣
ታግለን እናስቀራት ፍየሏን ለሀገር።”
ብለው በመደምደም ፍርዳቸውን ሰጡ፣
እንደ ፈራጁ እንጂ መች እንዳመጣጡ።





# ፍርድ እንደ ፈራጁ



ለአቶ መለስ ዜናዊ፡-

“ባሕር አቋረጠች ተሻግራ በረረች፣
ኧረ ምን ተሻለ ፍየሏ'ኮ ሄደች ?”
ብሎ ቢነግራቸው ለመለስ ዜናዊ፣
ትንታኔ ሰጡ እጅግ ዘመናዊ፡-
“ዶክተር ፕሮፌሰር ኢንጂነር ተብዬ፣
እናንተን ሳስረዳ አልቋል ጨዳራዬ፣
ዴሞክራሲያዊ መብቷ ስለሆነ፣
መንገዷ ጨርቅ ይሁን ሀሳቧ ከሆነ፣
ብለን አስበን ነው እኛው የለቀቅናት፣
ጠፍታ ልቧ ወልቋል ከፍተን በሸኘናት፣
ባቄላ ሲወደድ ፈስ ቀለለ እንዲሉ፣
ፍየሏም ስትወጣ ይረክሳል ቅጠሉ፣
ፍየል የሌላቸው ስንት ሃገራት አሉ፣
በኢኮሎሚያቸው አንቱ የተባሉ፣
አሁን አሳሳቢው ትኩረት የሚገባው፣
ፍየል ተደራጅታ እንዳትመለስ ነው፣
ስለዚህ አዲስ ሕግ በፓርላማው ፀድቆ፣
በሽብርተኝነት ማስፈረድ ነው አውቆ።”
ብለው በመደምደም ፍርዳቸውን ሰጡ፣
እንደ ፈራጁ እንጂ መች እንዳመጣጡ።

-----===-----

ከግርማ መንግሥቱ

gmgirma@yahoo.com